በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ PRESS RELEASE

# ዶ/ር ቴዎድሮስ የምረጡኝ ቅስቀሳ ተጠናክሮ ቀጥሏል

ለአለም አቀፍ የጤና ድርጅት ዳይሬክቶሬት ጄኔራልነት በመወዳደር ላይ ያሉት ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም የምረጡኝ ቅስቀሳውን አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ የአፍሪካ ካሪቢያንና ፓስፊክ ቡድን አባል አገራት ሙሉ በሙሉ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ቀደም ሲል የአፍሪካ ህብረት ለዶ/ር ቴዎድሮስ ሙሉ ድጋፉን መስጠቱ ይታወቃል፡፡ ሌሎች የደቡብ አሜሪካ የኤሽያና የአውሮፓ አባል አገራት ድምጽ ሊሰጧቸው እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ምርጫው የፊታችን ማክሰኞ ግንቦት 15 ቀን 2009 ዓ.ም በስዊዘርላንድ ዋና ከተማ ጄኔቭ የሚካሄድ ሲሆን የምርጫውን ሂደት የበለጠ ለማጠናከር አንድ የአገራችን ከፍተኛ የልዑካን ቡድን በቅርቡ ወደዚያው ያቀናል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ ይህንን ምርጫ ካሸነፉ በአፍሪካ የመጀመሪያው የአለም አቀፍ የጤና ድርጅት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይሆናሉ፡፡ ለዚህም በአገር ውስጥና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እየሰጡ ናቸው፡፡

ዶክተር ቴዎድሮስን ይህንን የአለም አቀፍ የጤና ድርጅት ይመራሉ ተብለው እምነት የተጣለባቸውና ተወዳዳሪዎቻቸውን በከፍተኛ ነጥብ በመብለጥ ከዚህ የመጨረሻው የምርጫ ጊዜ ከደረሱባቸው ምክንያቶች ዋነኛዎቹ በአገራቸው ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ በነበሩበት ወቅት በተለይም በጤና ጥበቃ ሚኒስትርነት ደረጃ በሰሩባቸው ጊዜያት በዘርፉ ባስመዘገቡት ውጤት በተለይም በእናቶች እና ህጻናት ሞት ቅነሳ እንዲሁም የወባ በሽታንና የልጅነት ልምሻን በአገራችን ለማጥፋት ባደረጉት ያላሰለሰ እንቅስቃሴ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተደማጭነትን አግኝተዋል ፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ደረጃ በሰሩባቸው ጊዜያትም ከተለያዩ አገሮቹ ጋር የተደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችና በዚህም የተመዘገቡ ውጤቶች ተቀባነት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ በተለያዩ ጊዜያት ላበረከቱት አስተዋጽኦ የተለያዩ አለም አቀፋዊ ሽልማቶችን አግኝተዋል፣ ሮተሪ የተባለ የአለም አቀፍ ድርጅት አገራቸውን ከልጅነት ልምሻ በሽታ ነጻ ለማድረግ ባደረጉት አስተዋጽኦ የፓውል ሃሪስ አዋርድ ተሸላሚ አድርጓቸዋል፣ የሴቶች ጤና በተለየ መንገድ እንዲጠበቅ ለማድረግ በሰሩት አበረታች ስራ The award for Perseverance እንዲሁም The American Society of Tropical Medicine and Hygiene የወባ በሽታ በህጻናቶች ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ በሚመለከት ላደረጉት ጥናት እውቅና ሰጥቷቸዋል፡፡

ዶክተር ቴዎድሮስ በዚህ ምርጫ አሸናፊ ከሆኑ ለአገራችን ፣ ለአፍሪካ እንዲሁም ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ አስቸጋሪና ውስብስብ የሆነውን የአለም አቀፍ የጤና ችግር ይፈታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃልአቀባይ ጽ/ቤት*

*ግንቦት 10 ቀን 2009 ዓ.ም*

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.